# ወዮላቸው ላፍቃሪያን

-በአበራ ለማ

ወዮላቸው ለፍቅረኞች፥ በጥልዬ አዚም ለማለሉ
በሱ ዜማ ግዳይ ጥለው፥ ፍቅር ወለላን ላበሰሉ፤
ወዮላቸው ለፍቅረኞች፥ ሰትሄድ ሰከተላቸን ለቀጸሉ
በጥሌ አስማት፥ ከሳት ላንቃው ለተደሉ
በፍቅር ሃረግ ተሳሰረው፥ አዲስ ጎጆን ለተከሉ፤
ወዮላቸው ወዮው...

ወዮላቸው ወዮው፥ ለእኒያ የዘመናችን አርበኞች
ላገር ፍቅር አቀንቃኞች፥ ለጥልዬ "ጎራው!..." ምርኮኞች፤
ወዮላቸው ወዮው፥ ለኒያ የጥበብ ማእድ ቤተኞች
አምበላቸውን ላጡት፥ የምዬ ጠቢያ ፈርጠች፤
ወዮላቸው ወዮው...

ወዮላቸው ወዮው፥ የፍቅር ሾተላይ ለገባቸው
"ሃርካ ፋኔ..." ላልቀናቸው፥ የጥሌ ትንፋሽ ለራቃቸው፤
ወዮላቸው ወዮው...
ወዮላቸው ወዮው...

*ለታላቁ ድምጻዊ ለዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ ሕልፈት መታሰቢያ
ሚያዝያ 12 ቀን 2001፥ ኖርዌይ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com